በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
**The Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**Ministry of Finance and Economic Development**

ቁጥር 7/ሕ/ል/መ/1/2/66
Ref.No

ቀን 05/07/2005
Date

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡ <u>መመሪያ ስለመላክ፤</u>

አዲሱ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶችን ሥራ ላይ ለማዋልና በነባር ስርዓቶች አፈፃፀም ላይ ለታዩ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት የተሻሻለ የውጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 768/2004 በተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከዚህ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተገናኙ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ መመሪያ እንደሚያወጣ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሠረት የተዘጋጀውን መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እየገለጽን መመሪያው ከመጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሶፍያን አህመድ
ሚኒስትር

ስልክ TEL 55 26 00, 22 66 98, 55 09 81 83,86,89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905, 1037
ፋክስ Fax 251-1-[illegible] 251-1-55 38 44
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

# የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ «መመሪያ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 35/2005» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ:-

1. አዋጅ ማለት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ነው::
2. «ባለሥልጣን» ማለት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው::
3. «ሚኒስቴር» ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው::
4. «ግብአት» ማለት ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ነው::
5. በዚህ መመሪያ ትርጉም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ::

## ክፍል ሁለት
## ቀረጥን ተመላሽ ስለማድረግ

### 4. ቅድመ - ሁኔታዎች

ቀረጥን ተመላሽ ለማድረግ የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው::

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ቀረጥ እንዲመለስለት ከሚያቀርበው ጥያቄ ጋር በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ የሚዘረዘሩ የወጪና ገቢ እና ሌሎች ሰነዶችን ደጋፊ በማድረግ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት::

2. የተጠየቀው ቀረጥና ቀረጡ ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት ጥሬ ዕቃ፣ አባቂ የምርት መገልገያ ወይም ሽቀጥ መጠንና አይነት በአዋጁ የተመለከተውን የሚያሟላ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት የተመላሽ ቀረጥ ጠያቂው ነው:: ጠያቂው ይህንን በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የራሱን ውሣኔ የመስጠት መብት ይኖረዋል::

3. የቀረበው የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ለሚያካሂደው ምርመራ ተመላሽ ቀረጥ ጠያቂው ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለበት::

## 5. <u>የጥሬ ዕቃ መጠቀሚያ ጊዜ ገደብ</u>

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባቸውን የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ የሚያቀርብባቸውን ግብአቶች ተጠቅሞ ያመረተውን ምርት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደውጭ አገር መላክ አለበት::

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ሊራዘም የሚችለው በአዋጁ በተቋቋሙት ሌሎች ሥርዓቶች በተደነገገው መሠረት ይሆናል:

## 6. <u>የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ የማቅረቢያ ጊዜ</u>

1. በቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ለገባ ጥሬ ዕቃ የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው እንደሁኔታው ምርቱ ወደ ውጭ በተላከ ወይም ጥሬ ዕቃው ለአምራቹ በቀረበ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው::

2. ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚቀርብ የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሲፈቅድ ይሆናል::

## ክፍል ሦስት
## የተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት

### 7. የተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች

በአገር ውስጥ በፈፀሙት ግዢ ላይ የከፈሉት ቀረጥ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው፡-

1. በወጪ ንግድ ሥራ ላይ በመሠማራት ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ለሚገኙ፣

2. በሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መመዘኛ መሠረት፣ ተገምግመው በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ ለተደረጉ፣ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች ይሆናል።

### 8. የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ አራት የተደነገገው ቢኖርም፣ የፈጣን ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ያመረቱት ሸቀጥ ወደ ውጭ መላኩን መጠበቅ ሳያስፈልግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 በተገለፀው መሠረት በአገር ውስጥ በገዙት ግብአት ላይ የከፈሉት ቀረጥ ይመለስላቸዋል። ሆኖም በአዋጁ በተፈቀደው ወይም በአዋጁ የተሰጠን ሥልጣን መሠረት በማድረግ በተራዘመው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአገር ውስጥ በገዙት ጥሬ ዕቃ ተጠቅመው ያመረቱትን ምርት እንደሁኔታው ወደ ውጭ መላክ ወይም በግብአትነት ለአምራች ላኪ ማቅረባቸውን በማረጋገጥ የቀረጥ ሂሣቡን የማወራረድ ግዴታ አለባቸው።

2. የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ለዚሁ ዓላማ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡት ሸቀጥ ማምረቻ እንዲውል በአገር ውስጥ በፈፀሙት የግብአት ግዥ ላይ ወይም ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ሸቀጥ ማምረቻ የሚያስፈልገውን ግብአት ለማምረት በአገር ወስጥ በፈፀሙት የግብአት ግዢ ላይ የከፈሉት ቀረጥ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ጥያቄያቸውን በየወሩ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላሉ።

3. ባለሥልጣኑ አመልካቹ በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን እንዲሁም ቀረጥ የተከፈለበትን ማስረጃ ትክክለኛነት በማጣራት ጥያቄው በቀረበ በበዛ በ7 ቀን ጊዜ ውስጥ የተከፈለውን የቀረጥ ሂሣብ ለአመልካቹ ተመላሽ ያደርጋል።

## 9. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

1. የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ከአገር ውስጥ በገዙት ግብአት ያመረቱት ምርት እንደሁኔታው ወደ ውጭ መላኩን ወይም ለአምራች ላኪ በግብአትነት መቅረቡን የሚያረጋግጥ ሪፖርት አዘጋጅተው በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚጠየቁ ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ የከፈሉት ታክስ ተመላሽ ከተደረገላቸው ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

2. ባለሥልጣኑ የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ያቀረቡትን ሪፖርት በማጠናቀር በየስድስት ወሩ ለሚኒስቴሩ እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 10. ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ ሂሣብ እንዲከፈል ስለማድረግ

የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 በተመለከተው መሠረት የተሟላ ሪፖርት ያላቀረቡ ወይም የቀረበው ሪፖርት በአገር ውስጥ በገዙት ግብአት ተጠቅመው ያመረቱት ምርት ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ወደ ውጭ መላኩን ወይም ለቀጥተኛ አምራች ላኪ በግብአትነት መቅረቡን የማያረጋግጥ ከሆነ ባለስልጣኑ ለውጭ ገበያ ባልዋለው ወይም ለቀጥተኛ አምራች ላኪ በግብአትነት ባልቀረበው መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(3) መሠረት ተመላሽ የተደረገውን ሂሣብ እንዲከፈሉ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የገቡትን ግዴታ ያልተወጡ የፈጣን ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በወንጀል ኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 11. ኦዲት ስለማድረግ

ባለሥልጣኑ የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎችን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ እና ከንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በመመርመር የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 12. የመብቱ መቋረጥ

የተፋጠነ ቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ቀጥተኛ አምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አመራች ላኪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(1) እና 9 የተመለከተውን ግዴታውን ካልተወጣ በአዋጁ የተመለከተው የወንጀል ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በስርዓቱ ተጠቃሚ የመሆን መብቱ ይቋረጣል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## በቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልሆኑ ላኪዎች መካከል <u>የሚኖር የግብአትና ያለቀለት ምርት አቅርቦት ትስስር</u>

### 13. <u>የአቅርቦት ትስስሩ የሚፈፀምበት ሥርዓት</u>

1. ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በአዋጁ የተዘረጉ ሥርዓቶች ተጠቃሚ ለመሆን በአዋጁ እና አዋጁን መሠረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተገለፁ ሁኔታዎችን /መስፈርቶችን/ ማሟላት አለባቸው::

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው በተጨማሪ ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ከቀጥተኛ ላኪው ጋር ያደረጉትን የዕቃ አቅርቦት ስምምነት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለባቸው:: ይህም ውል ከሌሎች መካከል ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ያመረተውን ጥሬ ዕቃ ወይም የመጨረሻ ምርት ለቀጥተኛ ላኪው ካስረከበ በኋላ በዚህ ጥሬ ዕቃ የተመረተውን እና ቀጥተኛ ላኪው የተረከበውን የመጨረሻ ምርት ወደ ውጭ የመላኩ፣ ካልተላከም ቀረጥና ታክሱን ከነመቀጮው የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ቀጥተኛ ላኪው መሆኑን መግለጽ አለበት::

3. ሚኒስቴሩ ጥያቄውን ከገመገመ በኋላ ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ጥሬ ዕቃውን ለማምረት ከውጭ በሚያስመጣው ጥሬ ዕቃ የሚመረተውን ምርት ዝርዝር (የግብአት ምርት ጥመርታ) እንዲሁም ሰርተፊኬት ይሰጣል:: ይህን መሠረት በማድረግ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ ለመመዝገብ የሚውል የቫውቸር ደብተር እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ በደብዳቤ ሲገልጽ በውሉ ስም ለተጠቀሰው ቀጥተኛ ላኪም በግልባጭ ያሳውቃል::

4. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ለቀጥተኛ ላኪው በስምምነታቸው መሠረት ጥሬ ዕቃውን (ምርቱን) ሲያቀርብ በአገር ውስጥ የሚከፈለውን ቀረጥ ከቀጥተኛ ላኪው መሰብሰብ አለበት:: ሆኖም ቀጥተኛ ላኪው የከፈለው ቀረጥ በአዋጁ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው::

5. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ጥሬ ዕቃዎቹን ወደ አገር ለማስገባት እንዲፈቀድለት ጥያቄ የሚያቀርበው የሚከተለውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ነው::

   ሀ. የማመልከቻው አቀራረብ እና የቫውቸር ፈቃድ አሰጣጥ አዋጁን ለማስፈፀም ሚኒስቴሩና ባለሥልጣኑ በሚያወጡት መመሪያ መሠረት ይከናወናል:: ሆኖም ከውጭ አገር ያስገባውን ጥሬ ዕቃ ባለበት ሁኔታ ለቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ላልሆኑ ላኪዎች የሚያቀርብ ጥሬ ዕቃ

አቅራቢ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለው በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በሚሰጠው ቫውቸር ዋጋ ልክ የኢንሹራንስ ቦንድ ሲያቀርብ ይሆናል::

ለ. የቫውቸር አሰጣጥ ለቀጥተኛ ላኪ የተዘረጋውን የቫውቸር አሰጣጥ ሥርዓት በመከተል በባለሥልጣኑ ይከናወናል::

ሐ. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ለቀጥተኛ ላኪው የሚያቀርበውን ግብዓት የሚያመርት ከሆነ በሥርዓቱ ተጠቅሞ ለዚሁ ዓላማ ያስገባቸውን ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም ያመረተውን ግብዓት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለቀጥተኛ ላኪው ማቅረብ አለበት:: በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም በባለሥልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር ቀረጥና ታክሱን ከነመቀጮው እንዲከፍል ይደረጋል::

መ. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ከውጭ የገዛውን ጥሬ ዕቃ ባለበት ሁኔታ በማብአትነት ለቀጥተኛ ላኪው የሚያቀርብ ከሆነ በስምምነታቸው መሠረት ጥሬ ዕቃው ወደ አገር በገባ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ጥሬ ዕቃውን ለላኪው ማስረከቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ ቫውቸሩ ተወራርዶ ለዋስትና የሰያዘው የኢንሹራንስ ቦንድ እንዲለቀቅለት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል:: ቀጥተኛ ላኪውም በዚህ ጥሬ ዕቃ የተመረቱ ምርቶችን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም የጉምሩክ ባለሥልጣን ጊዜውን አራዝሞ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ ካልላከ ቀረጡን ከነመቀጮው እንዲከፍል ይደረጋል::

6. ቀጥተኛ ላኪው በስሙ የኤክስፖርት ትዕዛዝ ኖሮት ነገር ግን የማምረቻ ድርጅት ሣይኖረው ሲቀርና ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪውን (ማምረቻ ያለውን) ሰው/ድርጅት ድጋፍ በሚፈልግበት ጊዜ:-

ሀ. ቀጥተኛ ላኪውን እና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪውን የሚያስተሳስራቸው የወጪ ምርቱን እንዲያመርትለት የተስማሙበት ስምምነት መኖር አለበት:: ሚኒስቴሩ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የሚውል የስምምነት ሞዴል ያዘጋጃል::

ለ. ቀጥተኛ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው (ምርቱን የሚያመርትለት) ስምምነታቸውን በመያዝ ቫውቸር ደብተር እንዲሰጣቸው በጋራ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው::

ሐ. የቫውቸር ደብተር ጥያቄ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ጥያቄ በሁለቱ መካከል ያለውን ስምምነት ወይም የአቅርቦት ትስስር የሚገልጽ መሆን አለበት። የቀረበው ማመልከቻም በሚኒስቴሩ ውሣኔ ይሰጥበታል።

መ. የቫውቸር ደብተሩም በቀረበው ስምምነት መሠረት ከሁለቱ ተዋዋዮች በአንዱ ስም ይሰጣል።

ሠ. ባለሥልጣኑ በአጥጋኝ መሠረት የጊዜ ገደቡ ለአንድ ዓመት እንዲራዘም ካልፈቀደ በስተቀር፣ ጥሬ ዕቃው አምራች ለሆነው ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ ከተላላፈበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሎ የተመረተው ምርት ወደ ውጭ መላክ ያለበት ሲሆን በመላኪያው ቢል ላይ የቀጥተኛ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪው ስም መስፈር አለበት።

ረ. ከሀገር ውስጥ ለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች የተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት ይጠበቅላቸዋል። ለዚህም ስምምነታቸውንና ዕቃው ወደ ውጭ የተላከበትን ማስረጃ ያቀርባሉ።

ሰ. ከዚህ በላይ በተራ ፊደል «ሠ» በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከውጭ በተገዛው ጥሬ ዕቃ ምርቱ ተመርቶ ወደ ውጪ ባይላክ መቀጮውን ጨምሮ ለሚከፈለው ቀረጥና ታክስ ቀጥተኛ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው።

7. በማናቸውም ምክንያት ከዚህ በላይ በአንቀጽ 11.6 በተገለፀው ሥርዓት ለመጠቀም የማይፈልግ ቀጥተኛ ላኪ በአማራጭ ከዚህ በታች በተመለከተው ሥርዓት መጠቀም ይችላል።

ሀ. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ቫውቸሩን ከቀጥተኛ ላኪው ጋር በጋራ ለመጠየቅ ፈቃደኛ ካልሆነ በአንቀጽ 11.2 እንደተጠቀሰው ሁለቱን የሚያስተሳስር ስምምነት ማቅረብ አለበት።

ለ. ቀጥተኛ ላኪው ስምምነቱን በማያያዝ በራሱ ስም ቫውቸር እንዲፈቀድለት ሚኒስቴሩን መጠየቅ አለበት።

ሐ. የማመልከቻው አቀራረብ ለዚሁ ተግባር የተዘረጋውን አሠራር በመከተል ይፈፀማል፡፡ ቫውቸሩም በባለሥልጣኑ የሚሰጠው ለቀጥተኛ ላኪው ብቻ ይሆናል፡፡ ቀጥተኛ ላኪውም ኤክስፖርቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ተራ ፊደል «ሠ» በተገለፀው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመፈፀም በግሉ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ፈቃዱ በሚኒስቴሩ ሲሰጠው ምርቱ ቀጥተኛ ባልሆነ አምራች ላኪው እንደሚመረት መግለጽ (ማመልከት) አለበት፡፡

መ. ምርቱን ለማምረት በሚያስፈልገው ከውጭ አገር በሚያስመጣው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ በቫውቸር እንዲከፈል በማድረግ ምርቱን አምርቶ ወደ ውጭ መላክ አለበት፡፡

8. ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች ከሀገር ውስጥ ለሚገዙት ጥሬ ዕቃ ተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት ይጠበቅላቸዋል፡፡ ለዚህም ስምምነታቸውንና ያመረቱትን ምርት ለቀጥተኛ ላኪ ያስረከቡበትን ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡ ሆኖም ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሥርዓት ተጠቃሚ ከሆነ ተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት አይኖረውም፡፡

## 14. <u>የዕቃ ማሸጊያና መጠቅለያ አምራች ኢንዱስትሪዎች</u>

1. የዕቃ ማሸጊያ ወይም መጠቅለያ አምራች ኢንዱስትሪዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቅመው ባስገቡት ጥሬ ዕቃ ያመረቱትን ሸቀጥ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ለሆነ ቀጥተኛ አምራች ላኪ የሚያቀርቡ ከሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው የትስስር ሥርዓት በመጠቀም ባስተላለፉት ግብአት መጠን ነፃ የሆኑትን ቀረጥ ወደ ቀጥተኛ አምራች ላኪው ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡ ቀረጡን የማወራረድ ኃላፊነት የቀጥተኛ አምራች ላኪው ይሆናል፡፡

2. የዕቃ መሸጊያ ወይም መጠቅለያ ምርቱ የቀረበው ለላኪ ከሆነ፣ ምርቱ ወደውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ለማሸግ ወይም ለመጠቅለል ጥቅም ላይ ሳይውል ቢቀር ሊከፈል ለሚገባው ቀረጥ በሁለቱ መካከል ባለው ውል መሠረት አምራቹ ወይም ላኪው የኢንሹራንስ ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. የተያዘው ዋስትና ሊለቀቅ የሚችለው ላኪው የዕቃ መሸጊያ ወይም መጠቅለያ ምርቱን ወደውጭ ለላከው ሸቀጥ ማሸጊያ ወይም መጠቅለያ ጥቅም ላይ ማዋሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡

# ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. **የተሻሩ መመሪያዎች**

1. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አፈፃፀም የሚመራበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 22/2000፣

2. በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች የከፈሉት ታክስ በተፋጣነ አኳኋን እንዲመለስ ለማድረግ የወጣው መመሪያ ቁጥር 26/2001 ተሽረዋል።

16. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ.ም

ሱፊያን አህመድ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Industry

ቁጥር 02·1·13/164
Ref. No

ቀን 05 መጋቢት 2005
Date

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- **የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ስለመላክ፤**

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መውጣቱ የሚታወስ ሲሆን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም አዋጁን ለማስፈጸም መመሪያ እንደሚያወጣ ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሠረት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶችን ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ የተዘጋጀ ስለሆነ የሚመለከታችሁ አካላት ይህንኑ አውቃችሁ መመሪያውን ሥራ ላይ በማዋል ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ እንድታደርጉ እየጠየቅን፤ የመመሪያውን ኮፒ 29 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ መላካችንን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ሰይድ ገመቹ ኢዶ
ሚኒስትር ዴኤታ

እንዲያውቁት፤

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት

  ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ግልባጭ፤

ለሴክተራል ግንኙነት፣ምክክርና ማበረታቻ ዳይሬክቶሬት
ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ስልክ 0115 50 92 71
0115 15 80 35
ፖ.ሣ.ቁ. 6945
Fax 0115 15 82 53
0115 53 49 69
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethiopia

# በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

## የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ሪከርድና ማህደር
Record & Archive
Ministry of Indus[illegible]

መጋቢት 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

   የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተሻሻለው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 6 (2)፣ 9 (1)፣ 11 (2)፣ 13 (2)፣ 15 (2)፣ 17(1 እና 2)፣ 22(1 እና 2)፣ 23(3)፣ እና አንቀጽ 28 (2)፣ የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነት ለማስፈጸም ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. **ዓላማ**

   የዚህ መመሪያ ዓላማ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ በወጪ ንግድ በመሳተፍ በሥርዓቱ ተጠቃሚ ለሆኑት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት፣ የወጪ ንግድ ግኝትን ለማሳደግ፣ በወጪ ንግድ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚሳተፉት የተጠናከረ ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ለአገሪቱ የበለጠ ጥቅም እንዲያስገኙ ለማስቻል፣ ገቢ ዕቃዎችን የመተካት አቅም ያላቸውን ድርጅቶች በመለየት ትስስር እንዲፈጥሩና አቅም እንዲገነቡ ለመደገፍ እንዲሁም የተዘረጉት ስርዓቶች በአግባቡ ተግባር ላይ መዋላቸውንና ተገቢውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለመከታተልና ለማረጋገጥ ነው።

4. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ነው።

   2. "የምስክር ወረቀት" ማለት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተመለከቱ መመዘኛዎችን አሟልተው ለሚገኙ አምራች ላኪዎች፣ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፣ ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች እና ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች የሚሰጥ የየሥርዓቶቹ ተጠቃሚነት የዕውቅና ምስክር ወረቀት ነው።

3. "ተረፈ ምርት" ማለት በምርት ሂደት ውስጥ ዋናው ምርት ከተመረተ በኋላ የሚቀረው ዝቃጭ ወይንም ቁርጥራጭ ማለት ነው።

4. "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደአስፈላጊነቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ወይም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማለት ነው።

5. "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማለት ነው።

6. በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

5. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ መሠረት በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ለመጠቀም በሚፈልግ ማንኛውም አምራች ባለ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ባለ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ባለ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ቅድመ ሁኔታዎች</u>

6. <u>የተመላሽ ቀረጥ ተጠቃሚዎችን የግብዓት ምርት ጥመርታ ስለማጽደቅ</u>

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲፀድቅላቸው ለሚኒስቴሩ ጥያቄ ሲያቀርቡ ወደ ውጪ ስለተላከው ምርት ወይም ስላኪዎች ስለቀረበው የምርት ግብዓት መግለጫና ይኸንኑ ለማምረት የፈጀውን ጥሬ ዕቃ ዓይነትና መጠን የሚያመለክት ዝርዝር መረጃ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዙት በቅጽ 3 "ሀ" እና 4 "ሀ" እና "ለ" መሠረት ወይም በሁለቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

2. ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ሲዘጋጅ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፣

3. ገዥ ያጡ ምርቶች ወይም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቀረጥ ያልተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎችን ወይም ምርቶችን ለኤክስፖርት የማያገለግሉ ለመሆናቸው ከተጠቃሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን በማረጋገጥ መረጃውን ለባለሥልጣኑ ያስተላልፋል፣

7. <u>የተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች</u>

1. በአገር ውስጥ በሚገዙት ጥሬ ዕቃ ላይ የከፈሉትን ታክስ በተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተመላሽ የሚደረግላቸው ድርጅቶች ዝርዝር በሚኒስቴሩ ተለይቶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ይተላለፋል፣

2. የተፋጠነ የቀረጥ ተመላሽ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ዝርዝር ዝግጅት በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ለአገሪቱ የሚያስገኙትን የውጭ ምንዛሪ፣ የፋይናንስ መግለጫዎች ዝግጅትና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያላቸው ሪከርድ ከግምት ውስጥ ይገባል።

8. <u>የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት ሰርተፊኬት ለማግኘት መሟላት የሚኖርባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ወደ ውጭ የሚልኩ ወይም ለላኪዎች የሚያቀርቡ ሲሆን በሥርዓቱ ለመጠቀም ጥያቄ የሚያቀርቡ አምራች ላኪዎች፣ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፣ ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪዎችና ላኪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተው ሲቀርቡ ሚኒስቴሩ የቀረበውን መረጃ በማጣራት የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

ሀ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አንድ (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን በአመልካቹ ተሞልቶና በፊርማው ተረጋግጦ የቀረበ ግዴታ የተገባበት መግለጫና ማረጋገጫ፣

ለ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሁለት "ሀ" የተመለከተውን የድርጅቱን አጠቃላይ መግለጫ፣

ሐ/ ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የኢንቨስትመንት፣ የላኪነት ወይም የአስመጪነት ፈቃድ፣

መ/ አመልካቹ አዲስ ከሆነ አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሰጠ የኢንቨስትመንት የምስክር ወረቀት ወይም አግባብነት ያለው የንግድ ፈቃድ፣

ሠ/ ከግብዓት ምርት ጥመርታ በተጨማሪ በአገር ውስጥ የሚሸጥ ወይም ወደ ውጭ የሚላክ ተረፈ-ምርት ካለ ተረፈ-ምርቱን እና በተረፈ-ምርቱ ውስጥ ያለው ከውጭ የገባው ጥሬ ዕቃ ያለው ድርሻ የሚያሳይ መግለጫ በቅጽ "አምስት ሀ" ወይም "አምስት ለ" ወይም በሁለቱ መሠረት መቅረብ አለበት

ረ/ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፍ፣

ተ/ የድርጅቱ ሂሣብ በውጭ ኦዲተር የተመረመረ ከሆነ የሂሣብ መግለጫ ኮፒ፣

9. <u>የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ወይም የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

1. በእነዚህ ሥርዓቶች ለመጠቀም ጥያቄ የሚያቀርቡ ድርጅቶቹ ሙሉ በሙሉ ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩና በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ያልሆኑ መሆን ይኖርባቸዋል፣

2. ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ፣

3 አመልካቹ አዲስ ከሆነ አግባብ ካለው የመንግሥት መ/ቤት የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

4. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፍ፣

5. የድርጅቱ ሂሣብ በውጭ ኦዲተር የተመረመረ ከሆነ የሂሣብ መግለጫ ኮፒ፣

6. የስርዓቶቹ ተጠቃሚዎች ከላይ የተጠቀሱትንና በቅጽ አንድ (ሐ) እና ቅጽ ሁለት (ሰ) ላይ የተመለከተውን ግዴታ በመግባት እና የድርጅቱን አጠቃላይ መግለጫ በማቅረብ ማረጋገጫ ሲሰጡ የስርዓቶቹ ተጠቃሚነት ሰርቴፊኬት ይሰጣቸዋል፣

7. በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጣውን መስፈርት የሚያሟላ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይንም ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን በማሟላት ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን [illegible] ማግኘት እንዲችል በደብዳቤ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ይገለጽለታል፣

8. በቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ወይንም በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈልጉ አምራቾች የጥሬ ዕቃዎችን ዝርዝር በቅድሚያ የሚያቀርቡ ሲሆን የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲፀድቅላቸው ለሚኒስቴሩ ጥያቄ የሚያቀርቡት ምርት በኤክስፖርት ከተላከ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፣

9. በውጪ ምርቱና በግብዓት አጠቃቀም ላይ ለውጥ ከሌለ ኤክስፖርት ባደረጉ ቁጥር የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲጸድቅላቸው በየጊዜው ማቅረብ አይጠበቅባቸውም

10. <u>የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት የሚኖርባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

በዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑት አምራቾች ለሚያመርቷቸው ምርቶች በግብዓትነት የሚጠቀሟቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና ኮምፖኔንቶች ለማቅረብ ፍላጎት ያላቸው የውጭና የአገር ውስጥ ድርጅቶች ሆነው የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ናቸው።

1. አመልካቹ የውጭ ድርጅት ከሆነ ጥሬ ዕቃዎቹን ወይም ኮምፖኔንቶቹን ውጭ አገር በራሱ ድርጅት እያመረተ የሚገኝ መሆን ይኖርበታል። የአገር ውስጥ ድርጅት ከሆነ ከአምራቾቹ የውክልና የምስክር ወረቀት የሚያቀርብ መሆን ይኖርበታል፣

2. አመልካቹ የውጭ ድርጅት ከሆነ በዘርፉ እንዲሠማራ በኢንቨስትመንት ቦርድ የተፈቀደለት ስለመሆኑ ማረጋገጫ፣

3. የአገር ውስጥ ከሆነ ከንግድ ሚኒስቴር የንግድ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚያቀርብ መሆን ይኖርበታል፣

4. አመልካቹ የውጭ ድርጅት ከሆነ ኬሚካሎቹን ወይም ኮምፖነንቶቹን የሚያመርትበት፣

   ሀ) የኩባንያው ስም

   ለ) ያለበት አገርና ከተማ

   ሐ) አድራሻ ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢሜይል፣ ፖ.ሣ.ቁ.

መግለጫ ያቀርባል።

5. አመልካቹ አዲስ ካልሆነ ስበጀት ዓመቱ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣

6. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፍ ማቅረብ፣

7. ከዚህ ጋር አባሪ በተደረገው ቅጽ 1 "መ" መሠረት፡-

ሀ/ በአምራች ድርጅቶች በብዛት የሚፈለጉ፣ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟሉና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ማቅረብ የሚችሉና ለዚህም በቂ ክምችት የሚይዙ፣

ለ/ አቅራቢዎቹ የውጭ ድርጅቶች ከሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚፈጥሩ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑ እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ጥሬ ዕቃዎችን ከአገር አስወጥተው ለማስወገድ የሚችሉ፣

ሐ/ አቅራቢዎቹ የውጭ ድርጅቶች ከሆኑ በሂደት ጥሬ ዕቃዎችን ወይንም ኮምፖኔንቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት ፍላጎት ያላቸው እና ይህንንም በቀጣይ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መተግበር የሚጀምሩ፣

መ/ አቅራቢዎቹ ኬሚካልና ዳይስታፍ የሚያቀርቡ ከሆነ ዕውቅና ካለው ላቦራቶሪ የየኬሚካሎቹን የፍተሻ ውጤት የሚገልጽ ሰርቲፊኬት የሚያቀርቡና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ህጎችን የሚያሟሉ፣

ስለመሆናቸው ግዴታ የሚገቡ፣

8. የስርዓቱ ተጠቃሚዎች በዚህ አንቀጽ ከተራ ቁጥር 1-9 የተጠቀሱትንና በቅጽ 1(መ) ግዴታ በመግባት እና በቅጽ 2 (ሐ) ላይ የተመለከተውን የድርጅቱን አጠቃላይ መግለጫ በማቅረብ ማረጋገጫ ሲሰጡ የስርዓቱ ተጠቃሚነት ሰርቲፊኬት ይሰጣቸዋል፣

9. በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጣውን መስፈርት በማሟላት አስፈላጊውን የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ፈቃድ በባለስልጣኑ መ/ሥሪያ ቤት ሊሰጣቸው እንዲችል በደብዳቤ ይገለጻል፣

10. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት ፈቃድ ሲሰጥ ለንግድ ሚኒስቴር በማሳወቅ የንግድ ፈቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

11. የንግድ ፈቃድ ያገኘ የውጭ ድርጅት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ (L/C በመክፈት ወይም በሌላ የባንክ አገልግሎት ጥሬ ዕቃ እንዲያስገባ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያውቀው ይደረጋል፣

## ክፍል ሦስት
## በቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆኑ ላኪዎች መካከል የሚደረግ የአቅርቦት ትስስር

### 11. የአቅርቦት ትስስሩ የሚፈጸምበት የአሠራር ሥርዓት

1. ቀጥተኛ አምራች ላኪዎች ወይም ቀጥተኛ ላኪዎች እና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች በሥርዓቶቹ ለመጠቀም እንደአስፈላጊነቱ ሁለቱም ወይንም ከሁለቱ አንዱ በአዋጅ ቁጥር 768/2004 የተጠቀሱትንና በዚህ መመሪያ የተገለፁትን ሁኔታዎች (መስፈርቶች) በማሟላት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል፣

2. በዚህ መመሪያ ከተገለፁት መስፈርቶች በተጨማሪ ቀጥተኛ ባልሆነ አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ እና በቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ቀጥተኛ ላኪው መካከል የተፈረመ የአቅርቦት ውል ስምምነት መኖር አለበት፣ በስምምነቱ ከሚኘተቱት መካከል ቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ቀጥተኛ ላኪው በተረከበው ግብዓት የተመረቱ ምርቶች ወይም የተረከባቸው የተጠናቀቁ ምርቶች ወደ ውጭ የሚላኩ ስለመሆናቸው፣ ካልተላኩ ቀጥተኛ ያልሆነው አምራች ላኪው ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢው በግብዓቶቹ ላይ መክፈል የነበረበትን ቀረጥ በአዋጁ አንቀጽ 10 እና 25(2) መሠረት ከነቅጣቱ የመክፈል ኃላፊነት የቀጥተኛው ላኪ መሆኑንና ሌሎች በአዋጁ የተቀመጡት ቅጣቶች ተፈጻሚ እንደሚሆኑበት መጠቀስ አለበት፣

3. ቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ቀጥተኛ ላኪው የማምረት፣ የመላክ ፈቃድ ወይንም የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት ሰርቴፊኬት ሊኖረው ይገባል፣

4. ስምምነቱ በአምስት ኮፒ ተዘጋጅቶ በሁለቱ ድርጅቶች ተፈርሞና በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና ለሁለቱ ተዋዋዮች እንዲሁም በተደረገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርቱ ለመላኩ ክትትል እንዲደረግ ኤክስፖርቱን ለሚከታተል ድጋፍ ሰጪ ተቋም ወይም ሴክተር መስሪያ ቤት እንዲደርሱ ይደረጋል፣

5. በሁለቱ መካከል የተደረገ ውል ሳይጸድቅ የግብዓት ቅብብሎሽ ማድረግ አይቻልም፣

6. ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪው ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢው የሌሎች ስርዓቶች ተጠቃሚ ካልሆነና የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት ጥያቄ ካቀረበ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ጥያቄው ተገምግሞ ተገቢ ሆኖ ከተገኘ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

7. በቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆኑ ላኪዎች ትስስር ለወጪ ንግድ በተላኩ ምርቶች ላይ ሁለቱ ተዋዋዮች ለወጪ ንግዱ ያደረጉት አስተዋጽኦ ታይቶ መረጃው በድጋፍ ሰጪ ተቋማትና ሴክተር መ/ቤቶች ይያዛል፡፡ ይህም መረጃ በየወሩ ተጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ይላካል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. <u>የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶች ሰርቴፊኬት ስለማሳደስ</u>

1. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠቃሚዎች የስርዓቶቹን ተጠቃሚነት ሰርቴፊኬት ለማሳደስ በሚቀርቡበት ወቅት በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

2. ባለፈው ዓመት በሥርዓቶቹ ተጠቅመው ባስገቡት ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ ማወራረዳቸውን ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፣

3. የሥርዓቶቹ ተጠቃሚዎች ቀደም ሲል በፀደቀላቸው የጥሬ ዕቃ ዓይነትና የግብዓት ምርት ጥመርታ ይዘት ላይ ለውጥ አለማድረጋቸው ለሚኒስቴሩ ካረጋገጡ ሚኒስቴሩ ያለፈውን መረጃ መሠረት በማድረግ የምስክር ወረቀታቸው እንዲታደስ በማድረግ የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲያገኙ ያስተሳስራል፣

4. የስርዓቶቹ ተጠቃሚዎች የኤክስፖርት ምርት፣ የጥሬ ዕቃ ፍላጎት ዓይነት እንዲሁም የግብዓት ምርት ጥመርታ ቀመሩ ቀደም ሲል አቅርበው ከፀደቀላቸው ከተለወጠ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዙት ቅፆች የተመለከቱትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12(4) በተመለከተው መሠረት የቀረበውን መረጃ ሚኒስቴሩ ገምግሞ ካጣራ በኋላ ውጤቱን ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ያስተላልፋል፣

13. <u>ስለመረጃ አያያዝና ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

1. የቫውቸር፣ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን፣ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ እና ቦንድድ የማብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች ከውጭ የገቡ ወይም በአገር ውስጥ የተገዙ ጥሬ ዕቃዎችን አጠቃቀም አስመልክቶ በኮምፒውተር የታገዘ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፣

2. የቫውቸር፣ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን እና የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ዓመታዊ የኤክስፖርት ዕቅዳቸውን ለሚመለከተው ሴክተር መሥሪያ ቤት ወይንም ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

3. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ስለኤክስፖርት አፈጻጸማቸው እና ሥርዓቶቹ አተገባበር ለሚመለከታቸው ድጋፍ ሰጪ ኢንስቲትዩቶች፣ ዳይሬክቶሬቶችና ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በየወሩ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የሴክተር መሥሪያ ቤቶቹም ይህንኑ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በየሦስት ወሩ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

4. ሚኒስቴሩ ከባለሥልጣኑና ከድጋፍ ሰጪ አካላት የሚደርሱትን የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ መረጃዎች በየ3 ወሩ በማጠናቀር አፈጻጸሙን ይገመግማል።

5. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በስርዓቶቹ መጠቀም ሲያቆሙ፣ ድርጅቱን ለሌላ ማስተላለፍ ሲፈልጉ ወይንም ስርዓቱን መቀየር ሲፈልጉ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቅድሚያ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

14. <u>በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የገባ ጥሬ ዕቃ ወይም በጥሬ እቃው የተመረተው ምርት ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ወይም ድርጅት የሚተላለፍበት ሁኔታ</u>

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶችን በመጠቀም ከቀረጥና ታክስ ነፃ ከውጪ የገባ ጥሬ ዕቃ ወይንም በጥሬ ዕቃው የተመረተ ምርት ለሌላ ሥርዓቱ ተጠቃሚ ለማስተላለፍ ሲፈልግ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማሟላት ይገባዋል፡

1. የሚተላለፍለት/ተረካቢው/ ድርጅቱ በወጪ ንግድ ስራ የተሰማራ መሆን ይኖርበታል፣

2. በአስተላላፊውና በተረካቢው መካከል የተፈረመውን የሽያጭ ስምምነት ወይንም የማስተላለፍ ስምምነት ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ስምምነቱም በቀጥታ ሳኪና ቀጥተኛ ባልሆነ ሳኪ መካከል የሚፈረመውን ስምምነት ይዘት ሊኖረው ይገባል፣

3. በጥሬ ዕቃዎች የሚመረቱ የወጪ ምርቶች ለውጥ ካላቸው ተረካቢው የወጪ ምርቶቹን ዓይነትና የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረብ ይኖርበታል፣

4. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም ይህንኑ በማረጋገጥ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከአስተላላፊው የቫውቸር ዕዳ ተቀንሶ በተረካቢው ድርጅት የቫውቸር ዕዳ ውስጥ ለመመዝገብ እንዲችል ውሉንና የግብአት ምርት ጥመርታውን ያስተላልፋል፣

5. የተላለፈለት ድርጅትም ግብዓቶቹ የገቡበትን ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ወደ ውጭ መላክ ያለበት የጊዜ ገደብ ጥሬ ዕቃውን በተረከበ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

15. <u>በምርት ሂደት ስለሚደርስ የጥሬ ዕቃ ብክነት መጠንና የምርት ብልሽት</u>

1. ወደ ውጪ አገር የሚላክ የወጪ ምርትን ወይም ለሳኪው የሚቀርበውን ግብዓት ለማምረት በሚያስፈልግ ጥሬ ዕቃ መጠን ላይ እንደምርቱ ባህሪና ሁኔታ እስከ 7% (ሰባ በመቶ) የብክነት መጠን ጨምሮ በማስላት አምራቹ በሚያቀርበው ጥያቄ ውስጥ ማካተት ይችላል፣

2. በምርቱ የተለየ ባህሪ ምክንያት ከ7% (ሰባ በመቶ) በላይ የብክነት መጠን መጨመር ሲያስገድድ ሚኒስቴሩ ጉዳዩን መርምሮ ተጨማሪ የብክነት መጠን ሊፈቅድ ይችላል፣

3. በምርት ሂደት የተበላሹና ለውጭ ገበያ መላክ የማይችሉ እንዲሁም ወደ ውጭ ተልከው የተመለሱ ምርቶች ቀረጥ ተከፍሎባቸው አገር ውስጥ መሸጥ እንዲችሉ በሚመለከተው ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ወይም ሴክተር መሥሪያ ቤት ታይቶ የሙያ አስተያየት ቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ መረጃው ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንዲተላለፍ ይደረጋል፣

4. የጥሬ ዕቃ አጠቃቀም ከአንድ ዓመት በኋላ የማራዘም ጥያቄ እና ለወጪ ንግድ ገበተው የሚመለሱ ግብዓቶችን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ከሚመለከታቸው ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጋር በማረጋገጥ መረጃው ለባለሥልጣኑ ይተላለፋል፤

## 16. በአመልካቾች የሚቀርቡ መረጃዎችን ስለማረጋገጥ

1. በማንኛውም የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለመጠቀም ፈልገው የሚቀርቡ የአመልካቾች መረጃዎችን ትክክለኛነት ሚኒስቴሩ አስፈላጊውን ግምገማና ማጣራት አካሂዶ ያረጋግጣል፤

2. በአመልካቹ የቀረበው መረጃ ከመጽደቁ በፊት ሚኒስቴሩ ባደረገው ማጣራት መስተካከል ያለበት ወይም ያልተሟላ መሆኑን ከደረሰበት ይህንኑ ለአመልካቾቹ በማሳወቅ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ሊጠይቃቸው ይችላል፤

3. አመልካቾቹ ባቀረቡት መረጃ መሠረት ጥያቄያቸው ከተስተናገደና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከተላለፈ በኋላ በሂደት በተደረገ ማጣራት ቀርቦ የነበረው መረጃ የተሳሳተ ሆኖ ከተገኘ የስህተቱ ምንጭ ተጣርቶ ለእርምጃ አወሳሰድ የሚያመች መረጃ ከተያዘ በኋላ እንዲስተካከል ይደረጋል፤

## 17. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ዘመንና ክፍያ

1. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማውጣት ብር300 ለማሳደስ ደግሞ ብር150 የአገልግሎት ክፍያ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መክፈል ይኖርባታል፤

2. የምስክር ወረቀቱ በተሰጠ ወይንም በታደሰ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ድርጅቱ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቀርቦ አስፈላጊው ስርዓት ማከናወን አለበት፤

3. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠቃሚነት ልዩ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ወይም ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላል፤

4. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀቱን ስማሳደስ ለሚኒስቴሩ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ባለፈው ዓመት ለኤክስፖርት ምርቱ እንዲውል በሥርዓቶቹ አማካኝነት ከቀረጥ ነፃ ሆነው ከውጪ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎች በትክክል ሥራ ላይ ያዋሉ ስለመሆናቸው ወይም በመጋዘን የሚገኙ ስመሆኑ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፣

5. ሚኒስቴሩ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች አፈጻጸም በተመለከተ ያዘጋጀውን ሰነድ በአማርኛና በእንግሊዝኛ በማዘጋጀት ተጠቃሚዎች እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

## 18. ተመሳሳዮቻቸው አገር ውስጥ ስለሚመረቱ ግብዓቶች

1. ከውጭ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የተጠየቁት ግብዓቶች ተመሳሳዮቻቸው አገር ውስጥ በበቂ መጠን የሚመረቱና ጥራታቸው ከውጭ ከሚገባው የማያንስ እንዲሁም በዋጋ ከውጭ ከሚገባው የማይበልጥ መሆናቸው በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከተረጋገጠ ወይም አቅራቢው በማስረጃ በማስደገፍ ማቅረብ ከቻለ ግብዓቶቹ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ከውጭ እንዳይገቡ ሚኒስቴሩ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያስተላልፋል፣

2. ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ የሚያመርቱ ድርጅቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ሚኒስቴሩ በመለየት የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች አቅም የሚጎለብትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

## 19. ስለ አገር አቀፍ የግብዓት ምርት ጥመርታ

1. ለሁሉም የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች የሚያገለግል ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ስወጪ ምርቶች እስኪዘጋጅ ድረስ አምራቾች ወይም ላኪዎች የሚያቀርቡት የግብዓት ምርት ጥመርታ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተገመገመ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፣

2. ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲዘጋጅ የሚያስተባብር፣ የተዘጋጀውን መርምሮ ለሚኒስቴሩ የሚያቀርብ በሚኒስቴሩ አስተባባሪነት ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የተውጣጣ አባላትን የያዘ ኮሚቴ ይቋቋማል፣

3. በእያንዳንዱ የወጪ ምርት ካታጎሪ በሚመለከተው ሴክተር መ/ቤትና ተቋም የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተደርጎ የግብዓት ምርት ጥመርታ መረጃ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ይደረጋል፣ ለዋናው ኮሚቴ የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥ ሴክሰፐርት ባለሙያም እንዲመደብ ይደረጋል፣

4. ከሚመለከተው ሴክተር/የወጪ ምርት ምድብ/ካታጎሪ የዘርፍ ማህበር ተወካይ በዝግጅቱ እንዲሳተፍ ይደረጋል፣

5. የወጪ ምርቶች የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ መረጃዎችን በማሰባሰብና እንደ አስፈላጊነቱ የአመራረት ሂደቶችን በቦታው ተገኝቶ በማየት ጭምር ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታዎች ተዘጋጅተው ለሚኒስትሩ ቀርበው እንዲጸድቁ ይደረጋል፣

6. በየምድብ ወጪ ምርት የጸደቀው የግብዓት ምርት ጥመርታ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ሆኖ አገልግሎት ላይ እንዲውል ለአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች፣ ድጋፍ ሰጪ ተቋማትና የዘርፍ ማህበራት በየጊዜው እንዲተላለፍ ይደረጋል፣

7. የስርዓቱ ተጠቃሚዎችም እንዲያውቁ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድረ ገጽ ወይም ፖርታል ላይ እንዲጫን ይደረጋል፣

8. በተዘጋጀው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ወይንም አዲስ ወደ ወጪ ምርት የሚገቡ ምርቶች የግብዓት ምርት ጥመርታ እንዲዘጋጅላቸው የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በማንኛውም የዘርፍ ማህበር፣ ድጋፍ ሰጪ ተቋም ወይንም የስርዓቶቹ ተጠቃሚዎች በመረጃ በማስደገፍ ከማብራሪያ ጋር ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል፣

9. በአንቀጽ 19(8) ላይ የተመለከተው ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ኮሚቴው ተጨማሪ መረጃዎቹን በማሰባሰብና የቅሬታ አቅራቢውን መረጃና ማብራሪያ በመመርመር የማሻሻያ ሃሳብ ወይም የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

10. ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች የሚያገለግለው ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ሲዘጋጅ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

20. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል።

21. <u>መመሪያው በሥራ ላይ የሚውልበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

አዲስ አበባ መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም

መኮንን ማንያዘዋል
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር

<u>ቅጽ አንድ "ሀ"</u>

## <u>የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ቀጥተኛ ላኪዎች የሚገቡት የግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ</u>

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ______________________ በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር ________ በ ______________________ የሥራ መስክ የተሠማራሁ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ለወጪ ምርቶች ግብዓትነት የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችንና አላቂ የምርት መገልገያዎችን ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾች እና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ እመለክታለሁ።

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ወይም የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣

2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ፣

3. ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ ዓይነት ኤክስፖርት ለማደርጋቸው ምርቶች የሚያስፈልጉት ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ወደ ውጭ የምልክ መሆኑን፣

4. ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ አንድን የወጪ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው መጠን መሠረት መሆኑን፣

5. የቫውቸር ሥርዓትን በመጠቀም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትን እና በመመሪያው የተቀመጡትን ግዴታዎች ሁሉ ሳሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ።

የአመልካች ስም ______________________________________

ፆታ ____________

የድርጅቱ ስም ______________________________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ________________

የአባሪ ገጽ ብዛት __________

ፊርማ ____________

የድርጅቱ ማህተም ____________________

## ቅጽ አንድ "ሰ"

## የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ____________________ በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር ________ በ ____________________ የሥራ መስክ የተሰማራሁ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ያሰቀላቸው የወጪ ምርቶች ወይም ለወጪ ምርቶች በግብዓትነት የሚውሉ በከፊል የተዘጋጁ ምርቶች ወይም ጥሬ ዕቃውን ባለበት ሁኔታ ለላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ሳልሆን አምራች ላኪ ለማቅረብ የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችና አላቂ የምርት መገልገያዎች ከቀረጥ ከፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።

ማረጋገጫ፡-

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ወይም በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣

2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ፣

3. ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ ዓይነትና መጠን ለላኪው ለማቀርባቸው ምርቶች ማምረቻ የሚያስፈልጉት ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ቀጥተኛ ለሆነው ላኪ የማስረክብ መሆኑን፣

4. ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ አንድን ለላኪው የሚቀርብ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ መጠን መሠረት መሆኑን፣

5. ምርቶቹን ለላኪው ሳቀርብ በአገር ውስጥ በምርቶቹ ላይ ሊከፈል የሚችል ወይንም የተከፈለ የቀረጥ መጠን ለመግለጽ፣

6. የቫውቸር ሥርዓትን በመተጠም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ለሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ።

የአመልካች ስም ____________________

ጾታ ________

የድርጅቱ ስም ____________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ____________

የአባሪ ገጽ ብዛት ____________

ፊርማ ____________

የድርጅቱ ማህተም ____________________

## ቅጽ አንድ "ለ"

## የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ____________________ በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር ________ በ ____________________ የሥራ መስክ የተሰማራሁ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ያለቀላቸው የወጪ ምርቶች ወይም ለወጪ ምርቶች በግብዓትነት የሚውሉ በከፊል የተዘጋጁ ምርቶች ወይም ጥሬ ዕቃውን ባለበት ሁኔታ ለላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ላልሆነ አምራች ላኪ ለማቅረብ የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችና አላቂ የምርት መገልገያዎች ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

ማረጋገጫ፡-

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ወይም በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርግ ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ፣
3. ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ ዓይነትና መጠን ለላኪው ለማቀርባቸው ምርቶች ማምረቻ የሚያስፈልጉት ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ቀጥተኛ ለሆነው ላኪ የማስረክብ መሆኑን፣
4. ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ አንድን ለላኪው የሚቀርብ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ መጠን መሠረት መሆኑን፣
5. ምርቶቹን ለላኪው ሳቀርብ በአገር ውስጥ በምርቶቹ ላይ ሊከፈል የሚችል ወይንም የተከፈለ የቀረጥ መጠን ለመግለጽ፣
6. የቫውቸር ሥርዓትን በመቀበም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ____________________

ጾታ ________

የድርጅቱ ስም ____________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ____________

የስባሪ ገጽ ብዛት ____________

ፊርማ ____________

የድርጅቱ ማህተም ____________________

ቅጽ አንድ "ሐ"

## የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት እና የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ ወ/ት ______________________ በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር ______________________ በ ______________________ የሥራ መስክ የተሠማራሁ ሲሆን የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ የምልካቸውን ምርቶች ለማምረት የምጠቀምባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት ፈቃድ ለማግኘት እንድችል አመለክታለሁ።

ማረጋገጫ፡-

1. የማመርታቸውን ምርቶች ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ የምልክ መሆኔን፣
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ላደርግ፣
3. የቨውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣
4. ከውጭ የማስገባቸው ጥሬ ዕቃዎች ኤክስፖርት ለማደርጋቸው ምርቶች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ብቻ መሆናቸውንና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ወደ ውጭ የምልክ መሆኑን እንዲሁም ለምርቱ የሚያስፈልግ መጠን የሚያመለክት የግብዓት ምርት ጥመርታውን ምርቱ በተሳከ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በማቅረብ የማጸድቅ መሆኔንና አዲስ የወጪ ምርት ወይንም ግብዓት ለኤክስፖርት ተግባር ከዋለ ይህንኑ በየጊዜው ለማቅረብ፣
5. ሥርዓቱን በመጠቀም በኩል በአዋጁና መመሪያዎች የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ።

የአመልካች ስም ______________________

ፆታ ______________________

የድርጅቱ ስም ______________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ______________________

የአባሪ ገጽ ብዛት ______________________

ፊርማ ______________________

የድርጅቱ ማህተም ______________________

ቅጽ አንድ "መ"

**የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ**

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ ወ/ት ______________________ በግብር ከፋይ ቁጥር __________

በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር ______________ በ ______________________ የሥራ መስክ የተሰማራሁ ሲሆን በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት በዋናነት ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ጊዜ ወደ ውጭ የሚልኩ ድርጅቶች ምርት ለማምረት የሚጠቀሙባቸውን ጥሬ ዕቃዎችን፣ አክሰሰሪዎችና ኮምፓንንቶች ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው በማስገባት ለማቅረብ እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት ፈቃድ ለማግኘት እንድችል አመለክታለሁ።

ማረጋገጫ፡-

1. በብዛት የሚፈለጉ፣ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟሉና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ለማቅረብና ለዚህም በቂ ክምችት ለመያዝ፣
2. የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚፈጥሩ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ለመስጠት እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ጥሬ ዕቃዎችን ከአገር አስወጥቼ ለማስወገድ፣
3. ኬሚካልና ዳይስታፍ የማቀርብ ከሆነ እውቅና ካለው ላቦራቶሪ የኬሚካሎቹን የፍተሻ ውጤት የሚገልጽ ሰርቲፊኬት ለማቅረብ፣
4. በሂደት ጥሬ ዕቃዎችን ወይንም ኮምፖኔንቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት ይህንንም በቀጣይ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመጀመር፣
5. ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ህጎችን ላሟላ፣
6. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ላደርግ፣
7. ሥርዓቱን በመጠቀም በኩል በአዋጁና መመሪያዎች የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ።

የአመልካች ስም ______________________

ፊርማ ______________

የድርጅቱ ስም ______________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ______________

የአባሪ ገጽ ብዛት ______________

ፊርማ ______________

የድርጅቱ ማህተም ______________________

"ቅጽ ሁለት" (ሀ)

## የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ድርጅቱ አጠቃላይ መግለጫ

1. የድርጅቱ ስም ________________

2. የድርጅቱ ሙሉ አድራሻ

   ክልል ________ ዞን/ክፍለ ከተማ ________ ወረዳ ________

   ቀበሌ ________ የቤት ቁጥር ________ ስልክ ቁጥር ________

3. የድርጅቱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ________________

4. ድርጅቱ የተቋቋመበት ዘመን ________________

5. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የካፒታል መጠን ________

   ሀ/ ቋሚ የማምረቻ መሣሪያዎች ብር ________________

   ለ/ ሕንፃ ብር ________________

   ሐ/ የሥራ ማስኬጃ ብር ________________

   መ/ ሌሎች ብር ________________

   ድምር ________________

6. የድርጅቱ የተጣራ ሀብት ብር ________________

7. የድርጅቱ ሠራተኛ ብዛት ________________

   ሀ/ ቋሚ የፋብሪካ ሠራተኛ ወንድ ________ ሴት ________

   ለ/ ጊዜያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ ወንድ ________ ሴት ________

   ሐ/ ሌሎች ሠራተኞች ወንድ ________ ሴት ________

8. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የይዞታ ሁኔታ፣

   ሀ/ የግል ☐

   ለ/ የጋራ ☐

   ሐ) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ☐

   መ/ የጋራ ማህበር ☐

   ሠ/ የመንግሥት ☐

9. ድርጅቱ ቀጥተኛ ባልሆነ ወይም በቀጥታ ያገኘው የሁለት ዓመት የኤክስፖርት የሽያጭ

   ሀ) በቀጥታ ለውጪ ገበያ በማቅረብ በአሜሪካን ዶላር ________________

   ለ) ወደ ውጭ ለሚልክ በማቅረብ በብር ________________

   የድርጅቱ ባለቤት ስም ________________

   ፊርማ ________________

   ማህተም ________________

"ቅጽ ሁለት" (ለ)

## የቦንደድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ድርጅት አጠቃላይ መግለጫ

1. የድርጅቱ ስም ______________________
2. የድርጅቱ መ/ቤ አድራሻ ______________________
   የድርጅቱ አድራሻ ክልል ____ ዞን/ክፍለ ከተማ ______ ወረዳ ________
   ቀበሌ ________ የቤት ቁጥር ________ ስልክ ቁጥር ________
3. የድርጅቱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ____________
4. የተቋቋመበት ዘመን ______________
5. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የካፒታል መጠን ________
   ሀ/ ቋሚ የማምረቻ መሣሪያዎች ብር ______________
   ለ/ ሕንፃ ብር______________
   ሐ/ የሥራ ማስኬጃ ብር______________
   ሌሎች ብር__________
   ድምር ______________________
6. የድርጅቱ አሁን ያለው ሠራተኛ ብዛት ____________
   ሀ/ ቋሚ የፋብሪካ ሠራተኛ ወንድ ______ ሴት ________
   ለ/ ጊዜያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ ወንድ ______ ሴት ________
   ሐ/ ሌሎች ሠራተኞች ወንድ ______ ሴት ________
7. ድርጅቱ ሊፈጥር የሚችል ተጨማሪ የስራ ዕድል________
   ሀ/ ቋሚ የፋብሪካ ሠራተኛ ______________
   ለ/ ጊዜያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ______________
   ሐ/ ሌሎች ______________
8. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለበት የይዞታ ሁኔታ፡
   ሀ/ የግል ☐
   ለ/ የጋራ ☐
   ሐ) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ☐
   መ/ የጋራ ማህበር ☐
   ሠ/ የመንግሥት ☐
9. የድርጅቱ ዓመታዊ የውጭ ሽያጭ ዕቅድ ______________ የአሜሪካን ዶላር
   የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ/ባለቤት ስም ____________
   ፊርማ ____________
   ማህተም ______________________

"ቅጽ ሁለት" (ሐ)

**የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች ድርጅት**

**አጠቃላይ መግለጫ**

1. የድርጅቱ ስም ______________________
2. የድርጅቱ ሙሉ አድራሻ ______________________
   የድርጅቱ አድራሻ ክልል ________ ዞን/ክፍለ ከተማ ________ ወረዳ ________
   ቀበሌ ________ የቤት ቁጥር ________ ስልክ ቁጥር ________
3. የድርጅቱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ______________________
4. የተቋቋመበት ዘመን ______________________
5. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የካፒታል መጠን ______________________
   ሀ/ ቋሚ መሣሪያዎች ብር ______________________
   ለ/ ሕንፃ ብር ______________________
   ሐ/ የሥራ ማስኬጃ ብር ______________________
   መ/ ሌሎች ብር ______________________
   ድምር ______________________
6. ድርጅቱ አሁን ያለው ሠራተኛ ብዛት ______________________
   ሀ/ ቋሚ ሠራተኛ ወንድ ________ ሴት ________
   ለ/ ጊዜያዊ ሠራተኛ ወንድ ________ ሴት ________
   ሐ/ ሌሎች ሠራተኞች ወንድ ________ ሴት ________
7. ድርጅቱ አገር ውስጥ ማምረት ሲጀምር ሊፈጥር የሚችለው ተጨማሪ የስራ ዕድል
   ሀ/ ቋሚ የፋብሪካ ሠራተኛ ______________________
   ለ/ ጊዜያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ ______________________
   ሐ/ ሌሎች ______________________
8. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለበት የይዞታ ሁኔታ፤
   ሀ/ የግል ☐
   ለ/ የጋራ ☐
   ሐ/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ☐
   መ/ የጋራ ማህበር ☐
   ሠ/ የመንግሥት ☐
9. የድርጅቱ ዓመታዊ የውጭ ሽያጭ ______________________ የአሜሪካን ዶላር
10. በውጭ አገር የሚገኝ አምራች ድርጅቱ ወይም የወከለው አምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ

   ስም ______________________ አገር ______________________

   ከተማ ________ ስልክ ቁጥር ______________________

   የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ/ባለቤት ስም ______________________

   ፊርማ ______________________

   ማህተም ______________________

"ቅጽ ሶስት" (ሀ)

<u>ለቀጥተኛ ኤክስፖርት ከውጭ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረቢያ ቅጽ</u>

| ተራ ቁ. | የኤክስፖርት ምርት* | | ለወጪ ምርት የሚያስፈልጉ የጥሬ ዕቃ ዓይነት" መለኪያ እና መጠን | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | መለኪያ | የኤክስፖርት ምርቱን ለማምረት የሚያስፈልግ የውጪ ጥሬ ዕቃ ዓይነት | መለኪያ | አንድ የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልግ መጠን | በምርት ሂደት ሊባክን የሚችል ጥሬ ዕቃ መጠን በ%** | የግብዓት ምርት ጥመርታ |
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

*የምርቱ ስምና መለኪያው ምርቱ ወደ ውጭ ሲላክ ከሚመዘገበው ወይንም ከተመዘገበው ምርት ዓይነትና ስም ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት::

** ይህ የጥሬ ዕቃ ብክነት መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መቅረብ አለበት::

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም ______________ ፊርማ ________ ማህተም ______________

"ቅጽ ሶስት" (ለ)

## ቀጥተኛ ላልሆነ ኤክስፖርት ከውጪ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረቢያ ቅጽ

| ተራ ቁ | ለላኪው የቀረበ* | | አንድን ለቀጥተኛ ላኪ የቀረበ ምርት ለማምረት የሚያስፈልግ የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ | | | በምርት ሂደት የባከነ/ሊባክን የሚችል የጥሬ ዕቃ ግምት በ%** | የግብዓት ምርት ጥመርታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የግብዓት/ምርት ዓይነት | መለኪያ | የጥሬ ዕቃው ዓይነት | መለኪያ | መጠን | | |
| | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

* የምርቱ ስምና መለኪያው በአገር ውስጥ የሽያጭ ደረሰኝ ላይ ከሚመዘገበው ምርትና መለኪያ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው፡፡

** ይህ የጥሬ ዕቃ ብክነት መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መቅረብ አለበት፡፡

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም ____________________ ፊርማ __________ ማህተም ____________________

Leg-28

"ቅጽ አራት" (ሀ)

ለቀጥተኛ ኤክስፖርት ከአገር ውስጥ የሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረቢያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ወደ ውጪ የተላከው | | አንድን ወደ ውጭ የተላከውን ምርት ለማምረት የሚያስፈልግ የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ | | | በምርት ሂደት ሊባክን የሚችል ጥሬ ዕቃ መጠን ግምት በ%** | የግብዓት ምርት ጥመርታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምርት/ዕቃ ዓይነት | መለኪያ | ዓይነት | መለኪያ | መጠን | | |
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

*የምርቱ ስምና መለኪያው ምርቱ ወደ ውጭ ሲላክ ከሚመዘገበው ምርት ዓይነትና ስም ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

** ይህ የጥሬ ዕቃ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መቅረብ አለበት።

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም ______________ ፊርማ ________ ማህተም ______________

Leg-28

"ቅጽ አራት" (ለ)

ቀጥተኛ ላልሆነ ኤክስፖርት በአገር ውስጥ ለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ማቅረቢያ ቅጽ

| ተራ ቁ. | ለላኪው የቀረበው | | ለላኪ የቀረበውን ምርት ለማምረት የተጠቀመበት የውጭ ጥሬ ዕቃ | | | በምርት ሂደት ሊባክን የሚችል ጥሬ ዕቃ መጠን ግምት በ%** | የግብዓት ምርት ጥመርታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምርት/ዕቃ ዓይነት | መለኪያ | ዓይነት | መለኪያ | አንድን የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልግ መጠን | | |
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

* የምርቱ የጥሬ ዕቃው ስምና መለኪያው ምርቱ ወደ ውጭ ሲላክ ከሚመዘገበው ምርት ዓይነትና ስም ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

** ይህ የጥሬ ዕቃ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መቅረብ አለበት።

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም ______________ ፊርማ ________ ማህተም ______________

Leg-28

"ቅጽ አምስት ሀ"

## ለአገር ውስጥ ገበያ በሽያጭ ስለሚቀርቡ ተረፈ ምርቶች የቀረበ መግለጫ

| ተ.ቁ | ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ ተረፈ ምርት | | ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ከገባው ጥሬ ዕቃ ውስጥ ለተረፈ ምርት የዋለው ዓይነትና ድርሻ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | [illegible] | የጥሬ ዕቃው ዓይነት | መለኪያ | በጠቅላላው ከገባው ጥሬ ዕቃ ያለው ድርሻ በመቶኛ |
| | 01 | 02 | 04 | 05 | 09 |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም ______________ ፊርማ ________ ማህተም ______________

Leg-28

"ቅጽ አምስት ሀ"

**ለውጭ አገር ገበያ በሽያጭ ስለሚቀርቡ ተረፈ ምርቶች የቀረበ መግለጫ**

| ተ.ቁ | ለውጭ አገር ገበያ የሚቀርብ ተረፈ ምርት | | ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ከገባው ጥሬ ዕቃ ውስጥ ለተረፈ ምርቱ የዋለው ዓይነትና ድርሻ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | መለኪያ | የጥሬ ዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከገባው ጥሬ ዕቃ ያለው ድርሻ በመቶኛ |
| | 01 | 02 | 04 | 05 | 09 |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም __________ ፊርማ ______ ማህተም __________

Leg-28

"ቅጽ ስድስት"

## የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ስምምነት ሞዴል

ይህ ስምምነት በ------------------------------------------------ ከዚህ በኋላ ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ እየተባለ በሚጠራው እና በ------------------------------------------------ ከዚህ በኋላ ቀጥተኛ ላኪ እየተባለ በሚጠራው መካከል ዛሬ --------------------- ቀን --------- ዓ.ም በ--------------- ከተማ ተፈፀመ"

1. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ የውጭ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 768/2004 በተደነገገውና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች መሠረት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶቹን ተጠቅሞ ባስገባው ጥሬ ዕቃ የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች፣ ምርቶች ወይም ያስመጣቸውን ጥሬ ዕቃዎች ለላኪው ወይም ለአምራች ላኪው ለማቅረብ ተስማምቷል፡፡

| ተራ ቁ. | የጥሬ ዕቃው ዓይነት | መለኪያ | መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |

2. ቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ላኪው ከዚህ በላይ በተ.ቁ.1 የተዘረዘሩትን ግብዓቶች ተጠቅሞ የሚያመርተውን ምርት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተስማምቷል፡፡

3. ቀጥተኛ ያልሆነው አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢው ያመረታቸውን በተ.ቁ.1 የተዘረዘሩ ግብዓቶችን ወይም ጥሬ ዕቃውን ለቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ላኪው ካስረከበበት ቀን ጀምሮ ለእነዚህ ግብዓቶች ማምረቻ ከቀረጥ ነጻ በገዛቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል ለሚገባው ቀረጥና ታክስ ሙሉ ኃላፊነቱን ቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ላኪው ይወስዳል፡፡

4. ቀጥተኛ አምራች ላኪው ወይም ላኪው ቀጥተኛ ካልሆነው ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ የተረከባቸውን ግብዓቶች ተጠቅሞ የሚያመርታቸውን ምርቶች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ አገር በመላክ ቫውቸሩን ለማወራረድ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀጥተኛ ካልሆነው አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ በተረከበው ግብዓት የተመረተውን ምርት ካልላከ ቀጥተኛ ያልሆነው አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ጥሬ ዕቃዎችን ሲገዛ መክፈል የነበረበትን ቀረጥና ታክስ ለመክፈልና በአዋጁ የተደነገጉትን ለመፈጸም ግዴታ ገብቷል፡፡

5. ሁለቱ ተዋዋዮች ይህንን ውል እና የየምርታቸውን የግብዓት ምርት ጥመርታ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በማቅረብ የሀገሪ ገበያ ተረፍ ማበረታቻ ሥርዓቶቹ ተጠቃሚ ለመሆን ተስማምተዋል።

6 ምርቱ ለቀጥተኛ አምራች ባለሀ ወይንም ቀጥተኛ ባለሀ ሲተላለፍ በምርቶቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ወይንም የተከፈለውን የአገር ውስጥ ታክስ መጠን ለመግለጽ ተስማምተዋል።

ይህ ስምምነት በአምስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ለተዋዋዮች፣ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ለሚመለከተው ሴክተር ተቋም ይሰጣል።

__________________________

ቀጥተኛ ያልሆነ ባለ. ፊርማና ማህተም

__________________________

ቀጥተኛ ባለ. ፊርማና ማህተም

ምስክሮች

1. __________________________

2. __________________________

* በቀጥተኛ ባለሀ ቀጥተኛ ያልሆነ ባለ. መካከል የሚደረግ የአቅርቦት ስምምነት ሊያካትቱ የሚገባቸው ነጥቦች ሲሆኑ ሌሎችም እንደአስፈላጊነታቸው ተዋዋዮቹ ሊያካትቱ ይችላሉ።

** የግብዓቱ ዕቃው መጠን በውሉ እንዳይካተት ከተፈለገ "መጠን" የሚለውን ከስም ላይ መተው ይቻላል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ሪከርድና ማህደር
Record & Archive
Ministry of I...